ሰኔ 2003 ዓ.ም.

# የወጣቶችን ስደት ለማስቀረት ምን ማድረግ እንችላለን?

## ክፍል ሁለት

### ከሱመ

በክፍል አንድ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት፣ አከባቢው ወደ ምድረበዳነት በመቀየሩ፣ በአከባቢው ሰርተውና አርሰው ለመኖር ስላልቻሉና ፊት ለፊታቸው የሚታይ ተስፋ ስላጡ፣ የሚሰደዱት ወጣቶቻችን ስደት ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት ምን ማድረግ እንችላለን በሚሉ የመፍትሔ ሓሳቦች ላይ በበኩሌ ይሆናሉ ያልኩዋቸውን ሃሳቦች ማቅረቤ የሚታወስ ነው። በዚህ በሁለተኛና የመጨረሻው ክፍል፣ በኢትዮጵያ በአጠቃላይ የሰፈነው ኢፍትሃዊ ሁኔታን ለመሸሽ ወደ ተለያየ አቅጣጫ በመሰደድ ላይ ያሉ ወገኖቻችንን ስደት ለመቀነስ ብሎም ለማስቆም መውሰድ ስለሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ላይ አስተያየቴንና የመፍትሄ ሃሳቦቼን ለውይይት ይገፑ ቀርቢያለሁ።

ጊዜአቸው አብቅቶ በህዝብ ትግል የተወገዱትን የአፄ ኃ/ስላሴና የደርግ አገዛዞችን በድፍኑ አምባገነናዊ ነበሩ ብለን ብናልፋቸው፣ ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ስርዓት ለመመስረት ለ17 ዓመታት የደርግን አምባገነናዊ አገዛዝ ታግዬ በማስወገድ ዴሞክራሲያዊና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትን በኢትዮጵያ አስፍኛለሁ፣ የብሔር ብሔረ-ሰቦች መብትን አስከብሬያለሁ፣ በማለት ራሱን የሚያሸሞነምነው የኢህአዴግ አገዛዝ በሀገራችን ኢትዮጵያ በትረስልጣኑን ከጨበጠ በኋላ ባሉት 20 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያዊያን የስደት ሁኔታን ስንመለከት፣ ኢትዮጵያዊያን ባለፉት አምባገን አገዛዞች ዘመን ከነበረው በከፋና እጅግ በበዛ ቁጥር እየተሰደዱ እንደሆነ እንመለከታለን። በተለይ የኢሮቦች ስደትን ስንመለከት ደግሞ በደርግ አገዛዝ ዘመን የጀመረው የኢሮብ ወጣቶች ስደት ዛሬ በኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን በቁጥርም በዓይነትም እጅግ ብሶበት እየቀጠለ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ለኢትዮጵያዊያን በአጠቃላይና በተለይ ደግሞ ለኢሮብ ወጣቶች መሰደድ መሰረታዊ ምክንያት የኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ የሚከተለው የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲና የፖለቲካ ቅኝት እንደሆነ በጥር ወር ለወጣቶቹ ስደት ሶስቱ መሰረታዊ ምክንያቶች በሚል ርእስ ስር በጻፍኩት መጣጥፌ በዝርዝር ስላስቀመጥኩት እዚህ አልደግመውም። ስለሆነም ዛሬ ወደ ሌላ ዝርዝር ሃተታ ውስጥ ሳልገባ በቀጥታ የወጣቶቻችንን ስደትን ለመቀነስ ብሎም ለማሰቀረት ሁላችንንም በጋራ ሊያሰሩ ያስችላሉ ብዬ በምገምታቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ለማተኮር እሞክራለሁ። ምክንያቱም ይህ የወጣቶቻችን ለስደት የመዳረግ ችግር ከፖለቲካና ከቡድናዊ አስተሳስብ ፀድቶ እንደ የጋራ ችግራችን ተደርጎ መወሰድ አለበት የሚል እምነት ስላለኝ ነው።

ዛሬ በርካታ የኢሮብ ወጣቶችና ለአቅመ አዳም እንኳን ያልደረሱ ልጆች ጭምር አከባቢውን ለቀው ወደተለያየ አቅጣጫ እየተሰደዱ እንደሆነ ሁላችን የምናወቀው ሃቅ ነው።

- በርካታ ወጣቶችና ከዕድሜ በታች የሆኑ ሕፃናት ጭምር ወደ ኤሪትርያ በመሄድ በሻዕቢያ የሚደገፉ አገዛዙን በትጥቅ ትግል እናስወግዳለን የሚሉ ቡድኖች እየተቀላቀሉ ነው።
- ብዙ ቁጥር ያለቸው ወጣቶች ደግሞ ያገኙትን አጋጣሚ ሁሉ እየተጠቀሙ፣ ያለ የሌለ ገንዘብ ከዘመድ አዝማድ በማሰባሰብ እየከፈሉ፣ ወደ እስራኤልና የተለያዩ የዓረብ ሀገራት ህይወታቸውን ለከፍተኛ አደጋ በማጋለጥ በመሰደድ ላይ ናቸው።

ስለሆነም የወጣቶቻችን ወደ ተለያየ አቅጣጫ መፍለስ እንዲቆም ሁላችንም የየድርሻችን ለመወጣት ቆርጠን በአንድነት መነሳት ይኖርብናል። በርግጥ ይህ የወጣቶቻችን ስደት ከብዙ ዓመት በፊት የተጀመረ ሆኖ እያለ እስከዛሬ ምንም ሳናደረግ እንደዚሁ በዝምታና በከንፈር መጠጣ ብቻ መቆየታችን ትልቅ ስህተት ነው። አሁን እየጀመርነው ያለነው የመፍትሄ ፍለጋ ውይይት ገና ከዛሬ 20 ዓመት በፊት ልንጀምረው ችለን ቢሆን ኑሮ ብዙዎችን ሕይወት ለመታደግ እንችል እንደነበረ የሚያጠራጥር አይደለም። ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን ዝም ብለን በያለንበት ከመብከንከንና ከንፈር ከመምጠጥ አርፍዶም ቢሆን አንድ ነገር ማድረግ ተገቢም የያንዳንዳችን ግዴታም ስለሆነ ለመፍትሄ ፍለጋ የአገዛዙ ተቃዋሚ ሆኑ ደጋፊዎች፣ እንዲሁም ከየትም አይደለንም የሚሉ ወገኖች በዚህ ጉዳይ ላይ በጋራ መሥራት ይችላሉ/አለባቸውም እላለሁ። ስለሆነም ለውይይት መነሻነት/መንደርደሪያነት ይረዳ ዘንድ ለኔ የመሰሉኝ፣ አብረን ለማስራት ያስችሉናል የምላቸው የመፍትሄ ሃሳቦችን እነሆ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

## ሀ- ወጣቶቻችን በሻዕቢያ ወደሚደገፉ ቡድኖች እንዳይሄዱ፣ የሄዱትም እንዲመለሱ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች፣

1. ከሁሉ አስቀድመን እያንዳንዳችን የየራሳችንን እምነት እንደያዝን ከጥላቻ፣ ከስሜትና፣ ከቡድናዊ ወገንተኝነት ራሳችንን ነጻ በማውጣት የነዚህ ወጣቶች ችግርን እንደ ጋራ መወገድ ያለባቸው ማኅበራዊ ችግሮቻችን ቆጥረን ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ብሎም ለመፍታት በጋራ መሥራት መቻል አለብን። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እያንዳንዳችን ከጊዜያዊ ጥቅምና ፍርሃት ራሳችንን ነጻ በማውጣት፣ ከድርጅት ወይም ከቡድን በፊት ትልቁን ስእል <u>ኢሮብነትን</u> ብሎም <u>**ኢትዮጵያዊነትን**</u> በግልጽ ለማየት መቻል ይኖርብናል። ከጥላቻ፣ ከቡድናዊ አስተሳሰብ፣ ከግል ጥቅምና ፍላጎት በፊት የህዝብና የሀገር ጥቅምን ማስቀደም ከቻልን በየተኛውም የፖለቲካ ጎራ ብንሰለፍም እንኳ ትልቁን ስእል (<u>ኢሮብነት</u>) በግልጽ እንዳናይ የሚገድብንን ማንኛውም ኃይል ሆነ ሌላ ደንቃራ ነገር ቢኖር በቀላሉ ልናየውና በጋራም ልናስወግደው እንችላለን።
2. ወደ ኤሪትርያ በመሄድ በሻዕቢያ የሚታገዙትን ቡድኖች የሚቀላቀሉ ወጣቶችና ለዓቅመ-አዳም ያልደረሱ ሕፃናት እየወሰዱት ያለ የተሳሳተ እርምጃ ምን ያህል የገዛ ህይወታቸውን ወደ አላስፈላጊ አደጋ እያሰገቡ እንደሆነ፣ ለኢሮብ ህዝብ ሆነ ለአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ከሻዕቢያና በሻዕቢያ ከሚደገፉ ሃይሎች ምንም ዓይንት

በጎ ነገር ሊመጣ እንደማይችል በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተቃዋሚው ሆነ የአገዛዙ ደጋፊ በጋራ ያለመታከት ማስተማር መቻል አለበት።

3. ከንግዲህ በኋላ ተጨማሪ ወጣቶች ወደ ኤሪትርያ ሆነ ወደ ተለያዩ የዓረብ ሀገራት የማይሄዱበት ሁኔታ እንዲፈጠር የነዚህ ወጣቶች ችግር ትክክለኛ መንስኤዎች የሚያጠና፣ የሚከታተልና መፍትሄ የሚሰጥ <u>ከባለሙያዎች፣ ከወጣቶች፣ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከሃይማኖት መሪዎችና ከአከባቢው ባለስልጣናት የተውጣጣ ኮሚቴ</u> እንዲመሰረትና በአከባቢው ባለስልጣናት እውቅና አግኝቶ አስፈላጊ ባጀትም ተመድቦለት እንዲሰራ ለማስቻል መሥራት ከእያንዳችን የሚጠበቅ ግዳጅ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።
4. መስተካከል ያለበቸው ሁኔታዎች እንዲስተካከሉ ከተደረገ በኋላ ኤሪትርያ ውስጥ ያሉት ወጣቶችን በተለያየ መንገድ ለመድረስ መሞከርና ያለውን የተመቻቸ ሁኔታ እንዲያውቁትና ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ያልተቋረጠ ጥሪና ቅስቃሳ የማድረግ ተግባር መከናወን ይኖርበታል።

## <u>ለ. ገንዘብ በመክፈል ወደ እስራኤልና የዓረብ ሀገራት የሚሰደዱ ወጣቶችን ስደት ለማሰቀረት መወሰድ ያለባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች፣</u>

ከኢሮብ ጀምሮ እስከ እስራኤልና የዓረብ ሀገራት ድረስ በተደራጀ መልክ ወጣቶችን በሆነ ባልሆነ እያማለሉና እየደለለ ገንዘብ እያስከፈሉ የሚያጓጉዙ ነብሰበላ በሰው ሕይወት የሚነግዱ ቡድኖች መኖራቸውን በቅርቡ በኢ.መ.ተ.ማ (የኢሮብ መብት ተማጓች ማህበር) በኢሮብ ማብሎ ድረ_ገጽ (www.irobmablo.org) አማካይት ካሰራጨው መግለጫ ለማየት ችለናል። ኢ.መ.ተ.ማ በመግለጫው እንዳስቀመጠው እነዚህ በወጣቶቻችን ደም ለመክበር በሚራወጡ ነብሰበላ ነጋዴዎች ውስጥ የኢሮብ ብሄረሰብ ተወላጆችና ሌሎች ኢትዮጵያዊያንም እንዳሉበት ገልጿል። እነዚህ በወጣቶቻችን ደም ለመክበር የሚፈልጉ ነብሰበላዎች ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ፣ ካልሆነም አስፈላጊ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው መ.ኢ.ተ.ማ በመግለጫው ጥሪ አቅርቦ ነበር። የነዚህ ወጣቶች የመሰደድ ጉዳይና የነዚህ ነብሰበላዎች ሰው አመላላሾች ወንጀልን ማስቆም ግን ለመ.ኢ.ተ.ማ ለብቻው የሚተው ግዳጅ አይደለም፣ መሆንም የለበትም። ይህ የአገዛዙ ደጋፊና ተቃዋሚን ለይቶ የሚመለከት ሳይሆን የሁሉም የኢሮቦች የጋራ ግዴታና ሸክም ተደርጎ መወሰድ ያለበት ጉዳይ ነው። የወጣቶቻችንን ፍልሰት/ስደት ለመቀነስ ከፈለግን በግንባር ቀደም ልንዘምትበት ከሚገቡን ጉዳዮች የነዚህ ነብሰበላዎች እኩይ ተግባር ባስቸኳይ ማስቆም ግንባር ቀደሙ ነው። እኛ በአንድ ላይ ከተባበርን ደግሞ እንኳን ይህን ይቅርና ሌላውንም ልናደርግ እንችላለንና የኢሮብ ህዝብ በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ በሚደርሱበት ችግሮች ምክንያት የገባበትን ምስቅልቅል ሁኔታን ለመቅረፍ እንተባበር፣ አንድ ላይ እንስራ።

## የተጠቀሰውን ፍልሰት ለማስቀረት መወሰድ የሚኖርባቸው እርምጃዎች፡

1. በቡድን ሆነ በግለሰብ ደረጃ እነዚህ ለገንዘብ ሲሉ የገዛ ወገኖቻቸውን ለዓረብ ነብሰበላዎች እየሸጡ ያሉትን የኢሮብ ተወላጆች ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያዊያንን በተመለከተ አስቀድሞ በዚህ እኵይ ተግባር የተሠማሩትን ሰዎች በሚገባ መከታተልና ማጥናት ያስፈልጋል። በማስከተልም ለየግላቸው ከዚህ እኩይ ተግባር እንዲቆጠቡ አስፈላጊ ማስጠንቀቂያና ምክር በተናጠል ሊሰጣቸው ይገባል። በሚሰጣቸው ምክርና ማስጠንቀቂያ የማይመለሱ ከሆነና በዚህ እኵይ ተግባራቸው ከቀጠሉ በቀጥታ ለሚመለከታቸው አካላት በማሳወቅ እነዚህ ነብሰበላዎች ላይ አስፈላጊ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይኖርብናል።
2. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምንገኝ ወገኖች ወጣቱ ትውልድ ወደዚህ አደገኛ ሁኔታ ራሱን እንዳያስገባና ለነዚህ ነብሰበላዎች ሴራ ሰለባ እንዳይሆን በተገኘው አጋጣሚ ሁለ መተላለፍ ያለበትን መልእክት ሳንሰለች በቀጣይንት ልናስተላልፍላቸው ይገባል።
3. በሲናይና በየመን በረሃዎች በተለያዩ ህገወጥ ካምፖች ውስጥ በመሰቃየት ላይ ያሉ ወገኖቻችንን በተመለከተ ዓቅም በፈቀደ ሁሉ ያሉበትን ሁኔታ በየጊዜው በመከታተል ስለሁኔታቸው ዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ተሟጓች ድርጅቶች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ልዩ ልዩ አከባቢያዊ ሰብኣዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶችና መንግስታት በሚገባ እንዲያውቁትና አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወስዱ መጠየቅን እንደ አንድ ተልእኮ ለመውሰድ መቻል ይኖርብናል።
4. በተለያየ ክፍለዓለማት ተበታትነን ያለን ኢሮቦች ዘመኑ የፈጠረልንን ተክኖሎጂ በመጠቀም ስለ ችግሮቻችንና የመፍትሂ ሃሳቦች በግልጽ መወያየት መቻል አለብን። ለዚህ አሁን በቅርቡ የተከፈተው የኢሮብ ማብሎ ድረ-ገጽ እንደ አንዱ መገናኛ መድረክ ሆኖ ሊያገለግልን ይችላል የሚል እምነት ስላለኝ ድረ-ገጹን ለከፈቱ ወገኖች ምስጋና እያቀረብኩ፣ ድረ-ገጹን እንደ መገናኛና መወያያ መድረካችን እንጠቀምበት ዘንድ ፈቃደኛ እንዲሆኑ እግረ-መንገዴን እየጠየቅኩ፡ ሁላችንም በየውይይቱ ተሳታፊ እንድንሆን እጋብዛለሁ።

## መደምደሚያ፤

እኛ ኢሮቦች የፈለገው ድርጅት አባላት ወይም ደጋፊ እንሁን፣ ያለ ምንም ቅድመሁኔታ በኢሮብነታችን ብቻ በጋራ ልንሰራባቸው የሚገቡን አንገብጋቢ የጋራ ችግሮች አሉብንና ተቻችለን የጋራ ጥቅማችንን ለማስከበር እንሰባሰብ፡ የሰለጠነ ውይይት እናድርግ እላለሁ። ከበርካታዎቹ አስቸኳይ የጋራ ትኵረታችንን ከሚጠይቁ አንገብጋቢ ችግሮች ውስጥ የሚከተሉት ሶስቱ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ናቸው እላለሁ።

1. <u>በተለያየ ምክንያት አከባቢውን ለቀው በመውጣት ራሳቸውን ወደተለያየ ችግር እያስገቡ ያሉ ወጣቶቻችን ስደት እንዲቆም ማድረግ ፣</u>
2. <u>እስከ ዛሬ ለብዙ ዘመናት አንድነቱን ጠብቆ የኖረው የኢሮብ ብሄረሰብ የሚኖርበት መሬት ዛሬ ወደ ሁለት ሀገራት እንዲከፈል ያደረገው የሄጉ ውሳኔ እንዲቀለበስ መሥራት ፣</u>
3. <u>በግፈኛው የሻዕቢያ አገዛዝ የ1990 ዓ.ም. ወረራ ወቅት ተጠልፈው የተወሰዱብንና እስከዛሬ ድረስ መዳረሻቸው የማይታወቁ ወገኖቻችን ወደ ቤታቸው (ቀያቸው) እንዲመለሱ በጋራ መሥራት ናቸው።</u>

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ሁላችን በአንድነት ልንቆምና ልንታገል እንችላለን ባይ ነኝ።

እንግዲህ እኔ እንደ አንድ ዜጋ መጀመሪያ ለወጣቶቻችን ስደት ምክንያቶቹ ናቸው ያልኳቸውን በማስቀመጥ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ሁላችንንም ሊያስማሙ ይችላሉ የምላቸው ሃሳቦችና አስተያየቶች በሁለት ክፍል በመከፈል አቅርቤያለሁ። ለወደፊቱ በዚህ ዙርያ ሰፋ ያለ የሰለጠነ ውይይትና ክርክር ሊካሄድበት ይችላል ብዬም ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም መጣጥፎቹ በቀጥታ የሁላችን የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት ወንድሞችና እህቶችን ህይወት የሚመለከቱ ስለሆኑ በዚህ የወጣቶቻችን ጉዳይ ላይ በርካታ ሰው ይሳተፋል፣ የተለያዩ የመፍተሄ ሃሳቦችም ይፈልቃሉ፣ በመወያየትም ሁነኛ መፍትሔ ላይ እንደርሳለን ብዬ ስለማምን ነው።

እንግዲህ ሰው ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም ነውና እኔ የመሰለኝን ወርውሬ አለሁ። ከንግዲህ የቀረው የናንተው ጉዳይ ነው እያልኩ በሚቀጥለው በሌላ ርእስና በሌላ መጣጥፍ እስከምንገናኝ በቸር ሰንብቱ እላለሁ።

ሱመ ነኝ ከምድረ ዓረብ